ቀን Date 13 2017
ቁጥር Ref.No 3.4.2/11/18

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- **ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ መረጃ መላክን ይመለከታል**፤

በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አባሪ አንቀጽ 11 መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ከተደረጉት የተዘጋጁ ምግቦች አንዱ ወተት መሆኑን በመግለጽ ገንዘብ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/856 በቀን 23/11/2017 በተጻፈ የህግ ማብራሪያ ልኳል፡፡

በመሆኑም ሚ/መስሪያ ቤቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ከተደረጉት የተዘጋጁ ምግቦች አንዱ የሆነው ወተትን አስመልክቶ የሰጠውን የህግ ማብራሪያ ለታክስ አሰባሰብ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ 1 /አንድ/ ገጽ ኮፒ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

አሰላምታ ጋር

ኮሪት አሊ መሐመድ
የገ[illegible] ድጋፍ ቡድን
አስተባባሪ

ግልባጭ፤

- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
  ገቢዎች ሚኒስቴር

አባሪዎች፤

- ለትግራይ ገቢዎች ልማት ባለሥልጣን

  መቐሌ

- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ሰመራ

- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ባሕር-ዳር

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር የገቢዎች ቢሮ

  ፌንፌኔ

- ለሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ጅግጅጋ

- ለሲዳማ ብሔራዊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣን

  ሀዋሳ

- ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ

  ሚዛን አማን

- ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ

  አርባ ምንጭ

- ለማዕካላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ

  ቡታጅራ

- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለሥልጣን

  አሶሳ

- ለጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ባለሥልጣን

  ጋምቤላ

- ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ሐረር

- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

  አዲስ አበባ

- ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለሥልጣን

  ድሬዳዋ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን ሚያ ሸ ጸ 2017
Date
ቁጥር 3.1/44/18
Ref.No

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ ፡- <u>መረጃን ስለመላክ ይመለከታል፤</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በተጨማሪ እሴታ ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አባሪ አንድ አንቀጽ 11 መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ከተደረጉት የተዘጋጁ ምግቦች አንዱ ወተት መሆኑ ይታወቃል ፤ በዚህም ላይ ሚኒስቴሩ የሰጠውን የህግ ማብራሪያ በደብዳቤ ቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/856 ሐምሌ 23 ቀን 2017 ዓ.ም ለተቋማችን ልኳል።

በመሆኑም የተሰጠውን የህግ ማብራሪያ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለስልጣን እንዲያውቁት እንዲደረግ ለታክስ ማጣጣም እና ክልሎች ድጋፍ ይህ ደብዳቤ ግልባጭ መደረጉን እያሳሰብን ከሚኒስቴሩ የተላከውን ማብራሪያ 1 ገጽ ቅጂ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>
ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
ለታክስ ማጣጣም እና ክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
ለታክስና ጉምሩክ መረጃ የማብራሪያ የምክር አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
<u>የገቢዎች ሚኒስቴር</u>

ዮሴፍ ሽፈራው
የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
Web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

አባሪዎች

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለባሕርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- መቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ገቢዎች ሚኒስቴር



ታ/እገዛ-94
ቋሚ/ገ/ክ
ቁ/ዐ/1857
ሃ/ሚ/ሰ/ት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ታክ/ቁ/ር/856
ቀን / Date 23/11/2017

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ከመ/ቤታችን በወጡ ደብዳቤዎች መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ከፀደቀበት ከሰኔ 27 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1006/2016 በሌላ መመሪያ ወይም ሕግ እስከሚተካ ድረስ ተፈፃሚነቱ የሚቀጥል ስለመሆኑ የተገለጸውን በማስታወስ በመመሪያው ቁጥር 1006/2016 አባሪ አንድ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ከሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ውስጥ የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ወተት የሚገኝ ቢሆንም በተለምዶ ወተት ተብሎ የሚጠቀሱትን በታሪፍ መጽሐፉ ምዕራፍ 11 የሚመደቡትን የወተት ተዋፅኦ ያላቸው የተዘጋጁ የሕፃናት ምግብ ዝግጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ማብራሪያ ይሰጣችሁ ዘንድ ሚያዝያ 22 ቀን 2017 ዓ.ም በቁጥር 4/2098/17 በተፃፈ ደብዳቤ የጠየቃችሁትን ይመለከታል።

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1006/2016 መሰረት ከታክሱ ነፃ ተደርገው የተዘረዘሩ አቅርቦቶች በሙሉ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 ጋር በተያያዘው አባሪ አንድ እንዲተኩ ተደርጓል። በመሆኑም በደንቡ አንቀጽ 65(2) መሠረት በደንቡ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ደንቡን የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ በደንቡ የተሻረ መሆኑ ተደንግጓል። በመሆኑም የመመሪያ ቁጥር 1006/2016 ድንጋጌዎች በደንቡ የተሻረ በመሆኑ ደንቡ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ መመሪያው ተፈፃሚ አይሆንም።

በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አባሪ አንድ አንቀጽ 11 መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ከተደረጉት የተዘጋጁ ምግቦች መካከል ወተት አንዱ ነው። በዚህ አንቀጽ መሰረት ከታክሱ ነፃ የተደረገው የወተት ምርት የተዘጋጀ እና ለምግብነት ዝግጁ የሆነው ብቻ ነው። በመሆኑም በተፈጥሮ ወተት እና ለሕፃናት ጥቅም ላይ በሚውሉት የበለጸጉ የወተት ተዋጽዖዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ የታክስ ነፃ መሆን ተፈፃሚ መደረግ አለበት። በተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ አተረጓጎም መርህ መሰረት ከታክስ ነፃ የመሆን አንቀጾች ጠበብ ተደርገው መተርጎም ያለባቸው በመሆኑ በዚህ መሰረት ከታክሱ ነፃ መደረግ ያለባቸው በታሪፍ መጽሐፉ ምዕራፍ 19 የተመላከቱት የምግብ ዝግጅቶች ሁሉ ሳይሆን በዚህ ምዕራፍ የሚመደቡ የወተት ተዋፅኦ ያላቸው የተዘጋጁ የሕፃናት የምግብ ዝግጅቶች ናቸው።

ስለዚህ ለቀረበው ጥያቄ ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ማስተናገድ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፡-
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክተር ጄኔራል
ገንዘብ ሚኒስቴር

ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባባሉን መስል ሊሰፍሉ ናቸን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documents Center No.2